**የቆላስይስ እና ኤፌሶን ጥናት 4-**

**የጥናት ክፍል፡ ቆላስይስ 3፡ 5-17 ኤፌሶን 4 1--6 ፡20-32-5፡1-13**

በክርስቶስ ካገኘነው ማንነትና ከተደረገልን በጎነት እና ምህረት የተነሳ እግዚአብሔርም ሆነ ሰዎች ከኛ የሚጠብቁትን ዋና ዋና ነገሮች ወይም ለውለታው ያለንን ምላሻችንን በሚቀጥሉት ተከታታይ ጥናታችን ማየት እንጀምራለን፡፡

**ርዕስ፡ አዲሱና የአሮጌው ሰው**

በዚህ ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱ ቃላትን አንስታችሁ ተነጋገሩበት፡፡ ለምሳሌ መጠራት.....

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ለጥሪያቸው የሚገባ ምልልስ ምን ምን መሆን እንደሆነ ዘርዝሩ፡፡
2. ቆላስያስ 3 እና አፌሶን 4 ውስጥ ያሉትን የአሮጌ ሰው እና የአዲሱን ሰው መገለጫውችን ዘርዝሩ፡፡
3. በአዲሱና በአሮጌ ሰው መካከል ያለው ፍጭትና ጦርነት ምን ይመስላል?
4. ገዳይ አይታችሁ ታውቃላችሁ ገዳይንስ እንዴትስ ትገልጣላችሁ ?
5. የምንገድላቸውንና የምናስወግዳቸው ነገሮች ዘርዝሩ፡፡
6. እነዚህን የተዘረዘሩትን የምንገድልበትን መንገድ፣ የሞቱትና ያልሞቱትን የምንለይበት መንገድን ተወያዩበት፡፡
7. ልጅ ሆኖ አለመተዘዝ ይኖር ይሆን? ቆላ 3፡6
8. የእግዚአብሔር ቁጣ ምንድር ነው? ራዕይ 21፡8
9. የሚገፈፈው አሮጌው ሰውና የሚለበሰው አዲሱ ሰው ስለምን የሚናገር ይመስላል ተወያዩበት፡፡

**መተግበር (Application)**

- ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ምን አስተማራችሁ?
- በመግደልና በማስወገድ የኛ ድርሻ የሆነበት ምክንያት ለምንድርን ነው
- ያልሞቱና ነገ መልሰው ይገድሉናል የምትሉ ጠላቶቻችንን ዛሬ መለየት ችለናል

| **አሮጌው ሰው** | | **አዲሱሰው** | |
|---|---|---|---|
| **ቆላስይስ** | **ኤፌሶን** | **ቆላስይስ** | **ኤፌሶን** |
| ዝሙት | ዝሙት | ምህረት | |
| ርኩሰት | ርኩሰት | ርኅራኄ | ርኅራኄ |
| ፍትወት | የሚያሳፍር ንግግር | ቸርነት | ቸርነት |
| ክፉ ምኞት | የስንፍና ንግግር | ትህትና | ትህትና |
| መጎምጀት | መመኘት | የዋህነት | የዋህነት |
| ንዴት | ንዴት | ትዕግስት | ትዕግስት |
| ቁጣ | መቆጣት | ይቅርታ ማድረግ | ይቅር መባባል |
| ክፋት | ጩኸት | ፍቅር | ፍቅር |
| ስድብ | መሳደብ | ሰላም | ሰላም |
| የሚያሳፍር ንግግር | ክፉ ቃል | መስጋኘነት | እውነት |
| ውሸት | ውሸት | | |
| | መራርነት | | |
| | ዋዛ | | |
| | ስርቆት | | |
| | ክፉ ቃል | | |

Col.3:5 Mortify:- nekroo (GREEK) nek-ro'-o , to deaden, i.e. (figuratively) to subdue:--be dead, mortify.

በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤